# ሞጁል 13

## የታክስ አስተዳደራዊ እና የወንጀል ቅጣቶች

## እና

## ተያያዥ ጉዳዮች

ሚያዝያ/2018 ዓ.ም

# ይዘት

- ክፍል አንድ:-
- አጠቃላይ ሁኔታ

ዓላማ

ወሰን

ትርጓሜ

# ይዘት

- ክፍል ሁለት
- ከታክስ ጋር በተገናኘ የሚፈጠር አለመግባባት
- የግብር ከፋዩ መብትና ግዴታ
- የታክስ ሕጎችን አስቀድሞ መተርጎም

# ይዘት

- ክፍል ሶስት
- የታክስ አስተዳደር እና የወንጀል ቅጣቶች እንዲሁም ሽልማቶች
- ማጠቃለያ
- ማጣቀሻ

# 1.1. ዓላማ

## ❑ ዋና ዓላማ

➢ በታክስ አስተዳደር ሕጉ በመወያየት በሕጉ የተቀመጡ መብትና ግዴታዎችን እንዲሁም አለመግባባት ሲፈጠር ምን ምን መደረግ እናዳለበት በመለየት በታክስ ለሚፈጸሙ ቅጣቶች እንዲሁም ሽልማቶችን ይገልጻሉ፡፡

## ❑ ዝርዝር ዓላማ

✓ የታክስ ከፋዩን መብት እና ግዴታ ይለያሉ፤

✓ በታክስ ውሳኔ አለመግባባት ሲፈጠር በየደረጃው አቤቱታ የሚቀርብበትን ሂደት ይዘረዝራሉ፤

ዝርዝር ዓላማ...

- **በታክስ የሚፈጸሙ የአስተዳደራዊ እና የወንጀል ቅጣቶች እንዲሁም ሽልማቶች ዙሪያ ገለጻ ማድረግ ይችላሉ፤**
- **አስተዳደራዊ ቅጣት በከፊል/ሙሉ በሙሉ የሚነሳባቸውን እና የማይነሳባቸውን ምክንያቶች ይዘረዝራሉ።**

## 1.2. ወሰን

- **የሰነዱ ሽፋን፤** አዋጅ 983/2008፣ አስተዳደራዊ ቅጣት አወሳሰን መ.ቁ. 9/2011፣ የታክስ ውሳኔ ቅሬታ አጣሪ ጽ/ቤት አሠራር መ.ቁ. 171/2013፣ የታክስ አስተዳደራዊ ቅጣት አነሳስ መ.ቁ. 189/2017።

# 1.3. ትርጓሜ

- ይግባኝ ሊቀርብበት የሚችል ውሳኔ
- ከአቅም በላይ የሆነ ምክንያት

- **የሥልጠና ተሳታፊዎች**

- ሥልጠናው መሠረታዊ እንደመሆኑ ለግብር ከፋዩ እና በግብር ከፋዩ ድርጅት ለሚሠሩ በድርጅቱ ሠራተኝነታቸው የተረጋገጠላቸው ባለሙያዎች ይሰጣል፡፡

- **ጊዜ:-ሶስት ሰዓት/6፡00**

# 1.3. ትርጓሜ

- ይግባኝ ሊቀርብበት የሚችል ውሳኔ

- ከአቅም በላይ የሆነ ምክንያት

ትርጓሜ…

## ❑ ቅጣት

ቅጣት፡- ማለት ስልጣን በተሰጠው አካል በአንድ ጉዳይ የተከሰሰውን ተከሳሽ ጥፋተኛ መሆኑን ካረጋገጡ በኋላ በአጥፊው ላይ ስርአትን ተከትለው የሚወስዱት የእርምት እርምጃ ነው፡፡

በታክስ ህጋችን ላይ ለግብር ከፋዩ በግልጽ የተቀመጡ መብት እና ግዴታወች ያሉ ሲሆን ግብር ከፋዮች በህጉ የተሰጣቸውን መብቶች ሲጠቀሙ በተመሳሳይ ሁኔታ ህጉ የጣለባቸውን ግዴታወችም የመወጣት ኋላፊነት ይኖርባቸዋል፡፡

የተጣለባቸውን ግዴታወች በማይወጡበት እና ጥፋቶችን በሚፈፅሙበት ጊዜ ለአስተዳደራዊ እና ወንጀል ቅጣቶች ይዳረጋሉ፡፡

## ትርጓሜ…

- ጽኑ ሕመም
- ባለሥልጣን
- ኮሚሽን
- የታክስ ውሳኔ ቅሬታ አጣሪ ጽ/ቤት
- የታክስ ውሳኔ ቅሬታ አጣሪ ጽ/ቤት ኃላፊ
- ቡድን
- የታክስ ወኪልነት የሙያ ፈቃድ

# ክፍል ሁለት

## የታክስ ህግ ተገዥነት እና ከታክስ ህግ ጋር በተገናኘ የሚፈጠር አለመግባባት

## 2.1. የታክስ ህግ ተገዥነት
### 2.1.1. ለታክስ ህግ ተገዥ መሆን

**ምን ማለት ነው?**

- ለታክስ ህግ ተገዥ መሆን ማለት **በታክስ ህጎች ላይ የተቀመጡ ግዴታዎችን በፈቃደኝነት ለመወጣት መስማማት/ፈቃደኛ** መሆን ማለት ነው።



**በምን ይገለፃል? (4ቱ መሰረታዊ የግብር ከፋዮች ግዴታዎች)**

- በግብር ከፋይነት መመዝገብ - **ትክክለኛ ምዝገባ**
- ታክስን **በወቅቱና በትክክል ማሳወቅ**
- **ትክክለኛ መረጃ** ለታክስ ሰብሳቢ ተቋሙ **ማቅረብ/ማሳወቅ**
- ታክስን **በወቅቱና በትክክል በመክፈል**
- ለግብር አወሳሰን የሚረዱ የሂሳብ ሰነዶችን በአግባቡ መያዝ
- የተቀመጡ የተመለሸ፣ ኪሳራ የማሳወቅ መብቶችን በአግባብ መጠቀም
- ሌሎችም (መተባበር)

## 2.1.2. ለታክስ ህግ ተገዥ አለመሆን

**ምን ማለት ነው?**

- ለታክስ ህግ ተገዥ አለመሆን ማለት **በታክስ ህጎች ላይ የተቀመጡ ግዴታዎችን ለመወጣት ፈቃደኛ አለመሆን** ማለት ነው፡፡

**በምን ይገለፃል? (4ቱ መሰረታዊ የግብር ከፋዮች ግዴታዎች ባለመወጣት)**

- በግብር ከፋይነት **አለመመዝገብ**
- ታክስን **በወቅቱና በትክክል አለማሳወቅ**
- **ትክክለኛ መረጃ** ለታክስ ሰብሳቢ ተቋሙ **አለማቅረብ**
- ታክስን **በወቅቱና በትክክል አለመክፈል**
  - ሌሎች መገለጫዎች
  - የተሳሳተ መግለጫ መስጠት (ገቢን ማሳነስ እና ወጪውን ማብዛት)
  - የማይገባውን ተመላሽ መጠየቅ፣
  - አላግባብ በተደጋጋሚ ኪሳራ ማሳወቅ
  - ደረሰኝ አለመቁረጥ
  - የሽያጭ መመዝገቢያን ማሽን በአግባብ አለመጠቀም
  - ሌሎችም



| የህግ ተገዢነት ባህሪ ደረጃ | መስተንግዶ ስትራቴጂ |
| --- | --- |
| ለህግ ተገዥ ላለመሆን የወሰኑ | ስትራቴጂ |
| ለህግ ተገዥ መሆን የማይፈልጉ | ስትራቴጂ |
| ለህግ ተገዥ መሆን የሚጥሩ በተለያየ ምክንያት ግን የማይሳካላቸው | ስትራቴጂ |
| በፈቃዳቸው ለህግ ተገዢ የሆኑ | ስትራቴጂ |

## የህግ ተገዥነት ደረጃዎች/መገለጫዎች

## የህግ ተገዥነት ስትራቴጂ

ከፍተኛ

| የህግ ተገዥነት ደረጃዎች/መገለጫዎች | የህግ ተገዥነት ስትራቴጂ |
|---|---|
| ለህግ ተገዥ ለለመሆን የቆረጡ | ሙሉ የህግን አቅምን መጠቀም |
| ለህግ ተገዥ ያለሆኑ ትኩረት ቢሰጣቸው የሚያከብሩ | መለየትና መከላከል |
| ለህግ ተገዥ ለመሆን ፈልገው የማይሳካላቸው | ለህግ ተገዥ እንዲሆኑ መደገፍ |
| ለህግ ተገዥ የሆኑ | አሰራርን ማቀላጠፍ |

የተቋሙ ጥረት ሁሉም ግብር ከፋዮች ለህግ ተገዥ እንዲሆኑ መስራት ነው

የህግ ተገዥነት ወፊ

ዝቅተኛ

# የህግ ተገዢነት ባህሪ ደረጃ እና መስተንግዶ ስትራቴጂ

## 1. የግብር ከፋይ የህግ ተገዢነት ባህሪ ደረጃ

- የታክስ ህጉን እና መመሪያዎችን በጥንቃቄ አክብረው የሚተገብሩ እነዚህም
- ህግን አክብሮ መንቀሳቀስ የሞራል እና የስነ ምግባር ግዴታቸው መሆኑን አምነው የተቀበሉ እና
- ግብር መክፈል ለሀገር እድገት ጥቅም አለው ብለው የተቀበሉ፣

## 1. መስተንግዶ ስትራቴጂ

- ዋናው የትኩረት አቅጣጫ የሚሆነው ማሳተፍ፣ ማወያየት እና መደገፍ ነው፣
- የግብር ስርአቱን ቀላል እና ቀልጣፋ ማድረግ
- አስፈላጊውን እርዳታ እና ምክር መስጠት
- በተደጋጋሚ ሊፈጠሩ የሚችሉ ቀለል ያሉ ስህተቶችን በመለየት አስቀድመው እንዲረዱት በዌብ ሳይት መጫን
- ታማኝ ግብር ከፋይ በመሆናቸው እውቅና መስጠት፣

# የህግ ተገዢነት ባህሪ ደረጃ እና መስተንግዶ ስትራቴጂ

| 2. የግብር ከፋይ የህግ ተገዢነት ባህሪ ደረጃ | 2. መስተንግዶ ስትራቴጂ |
|---|---|
| ❑ ህግን አክብሮ ግብር ለመክፈል ፈቃደኝነትና ፍላጎት ያላቸው እና<br>❑ የህግ ግዴታቸውን ጠንቅቀው የማያውቁ ፣<br>❑ በትክክለኛው ለመክፈል የሚሞክሩ ነገር ግን የግብር ህጉን በትክክል ባለማወቅ በተሳሳተ መንገድ ግብር የሚከፍሉ፣ | ዋናው የትኩረት አቅጣጫ የሚሆነው ማሳወቅ፣ማስተማር፣መምከር እና መደገፍ፣<br>ህጉን እና አሰራሩን እንዲረዱት በቂ ስልጠና እና ትምህርት መስጠት፣<br>በማወያየት ያለባቸውን የህግ አረዳድ ችግር በመለየት ማስተማር እና የአሰራር መመሪያዎችን ማሻሻል፣<br>ግልጽ ባልሆኑ በተመረጡ ለስህተት የሚዳርጉ የታክስ ህጎችን ክፍተቶች በመለየት ማስተማር ብሮሸሮች አዘጋጅቶ መስጠት፣<br>የታማኝ ግብር ከፋይ አሰራሮችን ቤንች ማርክ እንዲያደርጉ ማስተዋወቅ፣<br>ስህተቶቻቸውን አምነው እንዲያርሙ እድል መስጠት፣ |

# የህግ ተገዢነት ባህሪ ደረጃ እና መስተንግዶ ስትራቴጂ

## 3. የግብር ከፋይ የህግ ተገዢነት ባህሪ ደረጃ

- የግብር ህጉን ክፍተት በመጠቀም ግብር የማይከፍሉ ወይም አሳንሰው ለመክፈል የሚሞክሩ ግን ጥቂት ትኩረት ቢሰጣቸው በቀላሉ የሚስተካከሉ፣

## 3. መስተንግዶ ስትራቴጂ

- ከህገወጥ ተግባራቸው እንዲታቀቡ የህግ ማስከበር አቅምን እና ታክስ ስርአቱን ፍትሃዊነት በጠንካራ የህዝብ ግኑኝነት ስራ በማስተዋወቅ የቅድመ መከላከል ስራ መስራት (deterrence)፣
- የማስጠንቀቂያ ደብዳቤዎችን መጻፍ፣
- የገንዘብ ቅጣት መጣል፣
- እንደየ ሥጋት ደረጃቸው በመለየት ኦዲት ማድረግ፣

# የህግ ተገዢነት ባህሪ ደረጃ እና መስተንግዶ ስትራቴጂ

## 4. የግብር ከፋይ የህግ ተገዢነት ባህሪ ደረጃ

- ❑ ሆን ብለው ግብርን ለመሰወር እና ለማጭበርበር የወሰኑ ግብር
- ❑ ለመክፈል ምንም አይነት ፈቃደኝነቱ የሌላቸው እንዲሁም
- ❑ ከግብር ስርአቱ ተሰውረው ንግድ የሚያከናውኑ ፣

## 4. መስተንግዶ ስትራቴጂ

- ጠንካራ ስጋት ስራ አመራር እና ኢንተለጀንስ ስራ በመስራት መለየት፣
- ኦዲት ማድረግ፣ ንብርት ማስከበር ወይም መውረስ
- ጠንካራ ምርመራ ስራ በመስራት በፍርድ ቤት ማስቀጣት
- በሙሉ አቅም የህግ ማስከበር ስራ በመጠቀም ህገ ወጥነት አክሳሪ መሆኑን በማሳየት፣

ማህረሰቡ ህገ ወጦችን የመለየት እና የማስቀጣት አቅማችንን እንዲረዳ በማድረግ የታክስ ስርአቱን ፍትሀዊነት ማረጋገጥ ፡፡

## 5. የህግ ተገዥነት ጠቀሜታ

### 1. ለመንግስት

- ከታክስ የሚሰበሰበው ገቢ ከፍተኛ ስለሚሆን የሀገርን ወጪ በሀገር ገቢ ለመሸፈን ያስችላል ፣
- የሀገር ዕድገትን እና ልማትን ለማፋጠን ይረዳል ፣
- የማህበረሰቡን ስልጣኔ ለማጐልበት የሚያስፈልግ አቅምን ይፈጥራል፣
- የመንግስትን ገቢ እና ማህበራዊ ልማትን ያሳድጋል፣
- በአለም አቀፍ ደረጃም ተቀባይነትን ይጨምራል፡፡

2. ለግብር ሰብሳቢ መስሪያ ቤቱ

- የግብር ከፋዮች የታክስ ግዴታን በራስ ተነሳሽነት የመወጣት አቅም ከፍተኛ ስለሚሆን በየጊዜው ለመሰብሰብ የሚጠበቀውን ገቢ ለመሰብሰብ ያስችላል፣
- የተቀላጠፈ አገልግሎት ለመስጠት ይረዳል ፣
- ለህግ ማስከበር እና ታክሱን ለመሰብሰብ የሚወጡ ወጪዎችን ይቀንሳል ፣
- የግብር አሰባሰብ ሥርአቱን ለማዘመን የሚያስችሉ ጉዳዮች ላይ አትኩሮ ለመሥራት የሚያስችል ጊዜ እና አቅም ይፈጥራል፣
- በግብር ከፋዩ እና በግብር ሰብሳቢው መካከል ጤናማ የሆነ ግንኙነት እንዲኖር ያደርጋል፣
- በተጨማሪም በመንግስት እና በህዝብ በኩል የተቋሙን ተአማኒነት እንዲጨምር ያደርጋል።

3. ለግብር ከፋዩ

- የግብር ግዴታቸውን በአግባቡ ሲወጡ መብታቸውን በአግባቡ እንዲጠቀሙና እንዲጠይቁ መንገድ ይከፍታል፣
- ለታክስ ህግ ተገዥ ባይሆኑ ኖሮ ሊያወጡ የሚችሉትን ጊዜና ወጪ ይቆጥባል፣
- የተቀላጠፈ መስተንግዶን እንዲያገኙ እና ተወዳዳሪነታቸው እንዲጨምር ያደርጋል፣
- በግብር ሰብሳቢው እና በማህበረሰቡ በኩል መልካም ስምን ያተርፋል፡፡

## 2.1.3. የህግ ተገዥነት ጠቀሜታ

**ለግብር ከፋዩ**

- የግብር መብታቸውን እና ግዴታቸውን በአግባቡ እንዲወጡ ይረዳል
- ከአላስፈላጊ ወጪ በማዳን ጊዜንና ገንዘብ ይቆጥባል /Tax Compliance Cost/
- መስተንግዶን ያቀላጥፋል
- መልካም ስምን ያተርፋል
- እና ሌሎችም

**ለመንግስት / ለሚኒስቴሩ**

- የሚጠበቀውን ገቢ በአግባቡ በመሰብሰብ የሀገርን ወጪ በሀገር ገቢ ለመሸፈን ያስችላል
- የተቀላጠፈ አገልግሎት ለመስጠት ይረዳል
- ለህግ ማስከበር እና ታክስን ለመሰብሰብ የሚወጡ ወጪዎችን ይቀንሳል /Tax Administration Cost/
- ትኩረትን ለህግ ተገዥ ባልሆኑት ለይ ለማተኮር ይረዳል
- እና ሌሎችም

# ክፍል ሶስት፡- የታክስ አስተዳደር እና የወንጀል ቅጣቶች



## 3. አስተዳደራዊ ቅጣቶችንና የወንጀል ኃላፊነቶችን የሚመለከቱ ጠቅላላ ድንጋጌዎች

- አንድን ድርጊት መፈጸም ወይም አለመፈጸም **አስተዳደራዊ ቅጣት** እና **የወንጀል ኃላፊነት** የሚያስከትል በሚሆንበት ጊዜ ጥፋቱን የፈጸመው ሰው አስተዳደራዊ መቀጫ መቀጣቱ በታክስ አስተዳደር አዋጅ ከአንቀጽ **116 እስከ 133** የተደነገጉ **ወንጀል በፈጸም የሚያስከትሉ ተጠያቂነቶችን አያስቀርም፡፡**
- ማንኛውም ታክስ ከፋይ አስተዳደራዊ ቅጣት የተጣለበት እና/ወይም የወንጀል ክስ የቀረበበት መሆኑ **መክፈል የሚገባውን ታክስ የመክፈል ግዴታውን አያስቀርም፡፡**

# አጠቃላይ የቅጣት ጽንሰ ሀሳብ

- የወንጀልም ሆነ አስተዳደራዊ ቅጣት የሚጣለውና የሚወሰነው ጥፋት (Fault) በፈጸመ ሰው ላይ ነው፡፡
- ህግ በመተላለፍ (በመጣስ) የሚፈጸሙ ጥፋቶች <u>ሁለት ዓይነት ናቸው፡፡</u>

- <u>አስተዳደራዊ</u> ጥፋቶች በህግ የተደነገጉ <u>ግዴታዎችን ባለመፈጸም</u> (ባለመወጣት) የሚፈጸሙ ጥፋቶች ሲሆኑ
- <u>የወንጀል</u> ጥፋት ደግሞ በህግ <u>የተከለከሉ ድርጊቶች</u> (Prohibited actions) መፈጸም ወይም <u>አድርግ የተባለውን አለማድረግ</u> (Omission, Inaction, Negative action) ነው፡፡

# አጠቃላይ የቅጣት ጽንሰ ሀሳብ

➢ **<u>አስተዳደራዊ ጥፋት </u>** ተፈጽሟል ለማለት አንድ ሰው የህግ ግዴታ ያለበት መሆኑና ግዴታው በህጉ በተመለከተው **<u>ጊዜና ሁኔታ </u>**(Standard) አለመፈጸሙን ብቻ ማረጋገጥ በቂ ሲሆን የሚጠየቀው ሰው፡-

- ሊፈጽመው የሚገባ **በህግ የተደነገገ ግዴታ መኖሩ፣**
- **ግዴታውን የሚያመነጩት ህጋዊ ሁኔታዎች መሟላታቸው፣**
- ግዴታው ህጉ ባስቀመጠው **ጊዜና ሁኔታ** (Standard) መሰረት አለመፈጸሙ፣
- **ለጥፋቱ በህግ የተጣለ አስተዳደራዊ መቀጮ መኖሩ፣**
- መቀጮውን ለመወሰን የይርጋ ጊዜ የማይከለክል መሆኑ መረጋገጥ አለበት።

# አጠቃላይ የቅጣት ጽንሰ ሀሳብ

- ግዴታውን የሚያመነጩት ህጋዊ ሁኔታዎች መሟላታቸውን ለማረጋገጥ ህጉን በቅርበት በማየት ከቀረቡት ፍሬ ነገሮች ጋር ማገናዘብ ያስፈልጋል፡፡
- **በህግ ግዴታ የተጣለበት ሰው** ግዴታውን ያልፈጸመው ግዴታውን ባለመቀበል ላለመፈጸም ሆን ብሎ ወስኖ ወይም አስቦ ከሆነ የግዴታው አለመፈጸም የወንጀል ጥፋት የሚሆንበት ሁኔታ አለ፡፡
- አስተዳደራዊ ጥፋት መፈጸሙን ለማረጋገጥ ግን ግዴታው አለመፈጸሙን ብቻ ማረጋገጥ በቂ ሲሆን ግዴታው የተጣለበት ሰው ግዴታውን ያልፈጸመበት ምክንያትና የሀሳብ ሁኔታ በአብዛኛው ከግምት ውስጥ አይገቡም፡፡

# አጠቃላይ የቅጣት ጽንሰ ሀሳብ

የቀጠለ

➢ የወንጀል ጥፋት ተፈጽሟል ለማለት ሦስት ቅድመ ሁኔታዎች በአንድነት መሟላት አለባቸው ፡፡ ቅድመ ሁኔታዎቹ አንዳንድ ጊዜ አራት ይሆናሉ፡፡

- (Legal Element) የተፈጸመው ድርጊት እንዳይፈጸም በህግ የተከለከለ (Prohibited) ወይም ሳይፈጸም የቀረው ተግባር እንዲፈጸም በህግ የተደነገገ መሆን አለበት፡፡
- **(Mental Element (State of Mind))** ድርጊቱ የተፈጸመው ወይም ሳይፈጸም የቀረው ተግባር ያልተፈጸመው ሆን ተብሎ ወይም በቸልተኝነት መሆን አለበት፡፡

# አጠቃላይ የቅጣት ጽንሰ ሀሳብ

- **(Action or Omission)** ተከሳሹ ድርጊቱን በዋና አድራጊነት ወይም በተባባሪነት (ግብረ አበርነት) የፈጸመው ወይም መፈጸም የሚገባውን ተግባር በዋናነት ወይም በግብረ አበርነት ሳይፈጸም የቀረ መሆን አለበት።
- **(Cause and Effect)** የተፈጸመው ድርጊት ወይም ያልተፈጸመው ተግባር የማይፈለገውን ውጤት ያስከተለ መሆን አለበት። ውጤቱን ያስከተለው የተከሳሹ ድርጊት ወይም አለማድረግ መሆን አለበት።

# አጠቃላይ የቅጣት ጽንሰ ሀሳብ

የቀጠለ

ለምሳሌ፡-ህግ "ለተጨማሪ እሴት ታክስ የተመዘገበ ወይም መመዝገብ የነበረበት ማንኛውም ሰው ታክስ የሚከፈልበት የንግድ ስራ እንቅስቃሴ ሲያከናውን ለሚያከናውነው ለእያንዳንዱ ግብይት ግብይቱ በተከናወነበት ጊዜ የተጨማሪ እሴት ታክስ ደረሰኝ ለገዢው ወይም ለአገልግሎት ተቀባይ ያልሰጠ እንደሆነ ያለደረሰኝ በተከናወነው በእያንዳንዱ ግብይት ብር 50,000 የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል"

- ከላይ በተመለከተው የህግ ድንጋጌ ውስጥ ቅጣቱን ለመወሰን መሟላት ያለባቸው የህግ ቅድመ ሁኔታዎች፤

# አጠቃላይ የቅጣት ጽንሰ ሀሳብ

- ለተጨማሪ እሴት ታክስ የተመዘገበ ወይም መመዝገብ የነበረበት መሆኑ፣
- ግብይቱ የንግድ ሥራ እንቅስቃሴ መሆኑ፣
- የሚሰጠው ደረሰኝ የተጨማሪ እሴት ታክስ ደረሰኝ መሆኑ፣
- ደረሰኙ የሚሰጠው /የሚቆረጠው/ ግብይቱ በተከናወነበት ጊዜ መሆኑ፣
- ያለደረሰኝ ግብይት የተከናወነ መሆኑ፣
- ያለደረሰኝ የተከናወነው ግብይት ስንት እንደሆነ፣

# አጠቃላይ የቅጣት ጽንሰ ሀሳብ

➢ አስተዳደራዊ ቅጣት የገንዘብ መቀጮ ብቻ አይደለም።ከዚህ በታች የሚከተሉትም በአስተዳደራዊ ውሳኔ የሚጣሉ መቀጫዎች ናቸው ።

- የንግድ ድርጅትን (መደብርን) ማሸግ፣
- ፈቃድ ማገድ፣
- ፈቃድ መሰረዝ እና ሌሎችም ።

# አስተዳደራዊ ቅጣቶች

- ከምዝገባ እና ስረዛ ጋር የተያያዙ
- ሰነድ ባለመያዝ፣
- ታክስ በጊዜው ባለማስታወቅ፣
- ታክስ ዘግይቶ መክፈል፣
- ታክስ አሳንሶ ማስታወቅ፣
- ታክስን መሸሸ፡፡

# አስተዳደራዊ ቅጣቶች

## ከምዝገባ እና ስረዛ ጋር የተያያዙ ቅጣቶች
## (የታክስ አስተዳደር አዋጅ አንቀፅ 101)

# ከምዝገባ እና ስረዛ ጋር የተያያዙ ቅጣቶች (101)

1. በዚህ አዋጅ የተመለከቱት ሌሎች አስተዳደራዊ ቅጣቶች እንደጠበቁ ሆነው ማንኛውም ሰው በታክስ ከፋይነት መመዝገብ ሲገባው ያልተመዘገበ እንደሆነ መመዝገብ ከነበረበት ጊዜ ጀምሮ ለምዝገባ እስካመለከተበት ወይም በባለሥልጣኑ አነሳሽነት እስከ ተመዘገበበት ቀን ድረስ ባለው ጊዜ ውስጥ መክፈል ያለበትን ታክስ **25%** (ሃያ አምስት በመቶ) መቀጫ ይከፍላል።
2. ከላይ በተመለከተው ድንጋጌ መሠረት ታክስ ከፋዩ የሚከፍለው ታክስ የሌለ እንደሆነ መመዝገብ ከነበረበት ጊዜ ጀምሮ እስከ ተመዘገበበት ቀን ድረስ ላለው ለእያንዳንዱ ወር ወይም የወሩ ከፊል ለሆነ ጊዜ ብር **1,000(አንድ ሺ ብር)** መቀጫ ይከፍላል።

3. በተራ ቁጥር 1 መሠረት የሚጣለው መቀጫ በተራ ቁጥር 2 ከሚጣለው መቀጫ ያነሰ እንደሆነ በተራ ቁጥር 2 የተመለከተውን ለእያንዳንዱ ወር ወይም የወሩ ከፊል ለሆነ ጊዜ ብር **1,000(አንድ ሺ ብር) መቀጫ ይከፍላል።**

4. አስተዳደራዊ ቅጣቶችን ለመወሰን በወጣዉ ረቂቅ መመሪያ መሠረት **ከምዝገባ እና ስረዛ ጋር የተያያዙ ቅጣቶች ከንግድ ሥራ፣ ከቤት ኪራይ፣ ከመቀጠር ለሚገኙ የገቢ ዓይነቶች ተፈጻሚ ይሆናል።**

5. ከዚህ በላይ የተመለከተዉ ድንጋጌ በፌዴራል ታክስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 983/2008 አንቀጽ 107 መሠረት **አስተዳደራዊ ቅጣት ለሚጣልበት ለተጨማሪ እሴት ታክስ ምዝገባ ተፈጻሚ አይሆንም።**

6. ከላይ ለተመለከተዉ አፈጻጸም አስተዳደራዊ ቅጣቶችን ለመወሰን በወጣዉ መመሪያ መሠረት **"በቂ ምክንያት"** ማለት ታክስ ከፋዩ ታክስ የሚከፈልበት እንቅስቃሴ ካቆመ በኋላ ባሉት 30 ቀናት ታክስ ከፋዩ ሊያስወግዳቸው የማይችሉ በተፈጥሮ ወይም በሰው ሰራሽ ምክንያቶች የሚከሰቱ ማለትም በተወሰነ አካባቢ የተነሳ ወይም **የተፈጠረ ጦርነት፣ በእንቅስቃሴው ላይ አሉታዊ ጫና የሚፈጥ� ክስተቶች** (እንደ ዝርፊያ፣ ጐርፍ፣ ቃጠሎ፣ የመሬት መንቀጥቀጥ፣ መብረቅ፣ ተምች)፣ በታክስ ከፋዩ ወይም በታክስ እንደራሴ የተከሰተ የሚያስተኛ ጽኑ ህመም ወይም ሞት ነው፡፡

## ❑ ከታክስ ከፋይ መለያ ቁጥር ጋር የተገናኘ ቅጣት፤

- መለያ ቁጥሩን በታክስ ደረሰኝ፣ በታክስ ዴቢት/ክሬዲት ማስታወሻ፣ በታክስ ማስታወቂያ/ በሌላ በማንኛውም ሰነድ ላይ ሳይገልጽ የቀረ መለያ ቁጥር ባልተገለጸበት በእያንዳንዱ ሰነድ 3ሺ ብር ቅጣት ይከፍላል።
- መለያ ቁጥሩን አሳልፎ የሰጠም ሆነ የሌላን የተጠቀመ 10ሺ ብር ይቀጣል። በዚህ ምክንያት ያገኘው የገንዘብ ጥቅም 10ሺ ብር የሚበልጥ ከሆነ የሚከፍለው የገንዘብ ቅጣት መጠን ካገኘው ጥቅም ጋር እኩል ይሆናል።

# ሰነዶችን ባለመያዝ የሚጣል ቅጣት (102)

1. በታክስ ሕግ መሠረት መያዝ የሚጠበቅበትን **ማንኛውንም ሰነድ ያልያዘ** ታክስ ከፋይ በታክስ ሕጉ መሠረት ሰነዱ መያዝ በነበረበት **የታክስ ዘመን** መክፈል ያለበትን ታክስ **20% (ሃያ በመቶ) ቅጣት ይከፍላል።**
2. ሰነድ መያዝ ሲኖርበት ያልያዘ ታክስ ከፋይ ሰነዱን መያዝ በነበረበት **የታክስ ዘመን መክፈል የሚኖርበት ታክስ የሌለ እንደሆነ፡-**

# ሰነዶችን ባለመያዝ የሚጣል ቅጣት (102)

ሀ) **ለገቢ ግብር** ሲሆን ታክስ ከፋዩ የሂሳብ ሰነድ ላልያዘበት ለእያንዳንዱ የታክስ ዘመን **ብር 20,000 (ሃያ ሺህ ብር)** ፣ወይም

ለ) **ለሌላ ማንኛውም ታክስ** ሲሆን ታክስ ከፋዩ የሂሳብ ሰነድ ላልያዘበት የታክስ ዘመን **ብር 2,000 (ሁለት ሺህ ብር)** ቅጣት ይከፍላል።

# ሰነዶችን ባለመያዝ የሚጣል ቅጣት (102)

የቀጠለ

3. በተራ ቁጥር 1 መሠረት የሚጣለው መቀጫ በተራ ቁጥር 2 ከሚጣለው መቀጫ ያነሰ እንደሆነ የተራ ቁጥር 2 ፊደል "ሀ" እና "ለ" ድንጋጌ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

4. ማንኛውም ታክስ ከፋይ **ከሁለት ዓመት በላይ** የሂሣብ ሰነድ ካልያዘ ለታክስ ከፋዩ የንግድ ፈቃድ የሰጠው አካል ከባለሥልጣኑ በሚቀርብለት ማስታወቂያ መሠረት የታክስ ከፋዩን **የንግድ ፈቃድ ይሰርዛል፡፡**

# ሰነዶችን ባለመያዝ የሚጣል ቅጣት (102)

5. በንግድ ህግ ለተወሰነው የሰነድ መያዣ የጊዜ ርዝማኔ ወይም ሰነዶቹ አግባብነት በሚኖራቸው የታክስ ጊዜ የታክስ ማስታወቂያ ለባለሥልጣኑ ከቀረበበት ቀን ጀምሮ **ለአምስት ዓመታት** ሰነዶችን ይዞ ሳያቆይ የቀረ **የደረጃ ‘ሀ’** ታክስ ከፋይ **ብር 50,000 (ሃምሳ ሺህ ብር)** **ቅጣት ይከፍላል፡፡**

6. የሂሳብ መዛግብትን ይዞ የማቆያው ጊዜ እና የግብር ውሳኔን ለማሻሻል **ለሶስት ዓመት** ሰነዶችን ይዞ ሳያቆይ የቀረ መዝገብ የመያዝ ግዴታ ያለበት **የደረጃ “ለ”** ታክስ ከፋይ **ብር 20,000 (ሃያ ሺህ ብር)** **ቅጣት ይከፍላል፡፡**

**ምሳሌ 1፡-**የሂሳብ መዝገብ ማቅረብ የሚጠበቅበት ግብር ከፋይ የሂሳብ መዝገብ ያላቀረበና ሊከፍል የሚገባው የንግድ ትርፍ ግብር ብር 110,000 ቢሆን ቅጣቱን አስሉ?

**ምሳሌ 2፡-**

የሂሳብ መዝገብ ማቅረብ የሚጠበቅበት ግብር ከፋይ የሂሳብ መዝገብ ያላቀረበና ሊከፍል የሚገባው የንግድ ትርፍ ግብር ብር 80,000 ቢሆን ቅጣቱን አስሉ?

**<u>ለምሳሌ 1 መልስ</u>፡-**ንግድ ትርፍ ግብር 110,000 x 20% = 22,000 ቅጣት ይከፍላል ማለት ነው። ሆኖም ግን የሚከፍለው የንግድ ትርፍ ግብር የሌለ እንደሆነ ወይም ቅጣቱ ከብር 20,000 ያነሰ ቢሆን ብር 20,000 ይቀጣል ማለት ነው።

**<u>ለምሳሌ 2 መልስ</u> ፡-**

ንግድ ትርፍ ግብር 80,000 x 20% = 16,000 ይሆናል በመሆኑም በአዋጁ ንዑስ አንቀጽ 3 መሰረት ቅጣቱ ብር 20,000 ይሆናል ።

## የታክስ ማስታወቂያ ዘግይቶ ማቅረብ ስለሚያስከትለው ቅጣት (104)

1. በሕግ በተወሰነው ጊዜ ውስጥ የታክስ ማስታወቂያ ግዴታውን ያልተወጣ ታክስ ከፋይ ለዘገየበት ለእያንዳንዱ **የታክስ ጊዜ** ወይም ከፊል ለሆነው ጊዜ ያልተከፈለውን ታክስ 5% (አምስት በመቶ) 25% (ሃያ አምስት በመቶ) እስኪሞላ ድረስ መቀጫ ይከፍላል።

2. **ለመጀመሪያው የሂሣብ ጊዜ ወይም ከፊል ለሆነው ጊዜ** የታክስ ማስታወቂያ ያላቀረበ ሰው በተራ ቁጥር 1 ድንጋጌ መሠረት የሚከፍለው መቀጫ ከብር **50,000 (ሃምሳ ሺህ ብር) አይበልጥም።**

# የታክስ ማስታወቂያ ዘግይቶ ማቅረብ ስለሚያስከትለው ቅጣት (104)

3. ለዚህ አንቀጽ አፈጻጸም ያልተከፈለ ታክስ ነው የሚባለው በታክስ ማስታወቂያ ላይ መታየት በነበረበት እና ታክሱ መከፈል ባለበት ቀን በተከፈለው ታክስ መካከል ያለው ልዩነት ነው።

4. በማናቸውም ሁኔታ የሚጣለው መቀጫ ቀጥለው ከተመለከቱት ከዝቅተኛው ያነሰ አይሆንም፡-

ሀ) ብር 10,000 (አሥር ሺህ ብር) ፣

ለ) በታክስ ማስታወቂያ ላይ መመልከት ከነበረበት የታክስ መጠን 100% (መቶ በመቶ)

5. በዚህ አንቀጽ የተመለከተው ቢኖርም ታክስ ከፋዩ በታክስ ጊዜው ሊከፍል የሚገባው ታክስ የሌለ እንደሆነ ፣ የታክስ ማስታወቂያ ሳያቀርብ ለዘገየበት ለእያንዳንዱ የታክስ ጊዜ ብር (አሥር ሺህ ብር) መቀጫ ይከፍላል።

## የታክስ ማስታወቂያ ዘግይቶ ማቅረብ ስለሚያስከትለው ቅጣት

በአዋጁ አንቀጽ 104 የተደነገገው ቅጣት የታክስ ጊዜ ማለት በአዋጁ አንቀጽ 2(38) በተሰጠው ትርጉም መሰረት ሆኖ፡-

ሀ) የቅጣቱ አወሳሰን ለገቢ ግብር አዋጅ በዓመት፣

ለ) ለተጨማሪ እሴት ታክስ በየወሩ

ሐ) ከተከፋይ ሒሳብ ተቀንሶ የሚያዝን ታክስ /ከዕቃ ሽያጭና አገልግሎት ክፍያ የሚቀነስ ግብር፣ ከተቀጣሪ ክፍያ የሚቀነስ ግብር/ በሚመለከት በየወሩ፣

መ) ከተከፋይ ሂሳብ ተቀንሶ የተከፈለን ሳይጨምር የሠንጠረዥ "መ" ገቢ ሁለት ወር የሚሰላ ይሆናል።

- **ይህ አንቀጽ መዝገብ የመያዝ ግዴታ በሌለባቸው በደረጃ "ለ" ታክስ ከፋዮች ላይ ተፈጻሚ አይሆንም።**

## የታክስ ማስታወቂያ ዘግይቶ ማቅረብ ስለሚያስከትለው ቅጣት (104)

**ምሳሌ1፡-**አንድ ታክስ ከፋይ በታክስ ዘመኑ ያልከፈለው ወይም በቀሪነት የሚፈለገው የታክስ መጠን ብር 60,000 ቢሆንና የታክስ ማስታወቂያ ለ7 ወራት አዘግይቶ ያቀረበ ቢሆን አስተዳደራዊ መቀጫው ስንት ይሆናል?

- በድንጋጌው በንኡስ አንቀፅ 1 መሰረት ለ7 ወራት ቢዘገይም ቅጣቱ 25% እስኪሞላ ብቻ በመሆኑ **60,000*5ወር*5%= 15,000 ይሆናል፡፡**
- በድንጋጌው በንኡስ አንቀፅ 4 መሰረት የሚጣለው መቀጫ በማንኛውም ሁኔታ ቀጥሎ ከተመለከቱት **ከዝቅተኛው ያነሰ አይሆንም** በሚለው ድንጋጌ መሰረት
  - በንኡስ አንቀፅ “ሀ” መሰረት ብር 10,000
  - በንኡስ አንቀፅ “ለ” መሰረት ብር 60,000.00*100% = 60,000.00
- በዚህ መሰረት የሚጣለው አስተዳደራዊ መቀጫ በንዑስ አንቀጽ 1 መሰረት የተሰላው መቀጫ ከንዑስ አንቀጽ 4 ሲነጻጸር ብር 15,000 ከብር 10,000 የበለጠ እና ከብር 60,000 ያነሰ በመሆኑ ብር 15,000 ከዝቅተኛው ብር 10,000 ያነሰ **ባለመሆኑ** ብር 15,000 ለታክስ ዘመኑ ቅጣት ይከፍላል ማለት ነው፡፡

**ምሳሌ 2.** በታክስ ዘመኑ ያልተከፈለው ወይም በቀሪነት የሚፈለገው የታክስ መጠን ብር 20,000 ለ3 ወራት የታክስ ማስታወቂያ ሳይቀርብ የዘገየ ቢሆን አስተዳደራዊ መቀጫው ስንት ይሆናል?

የቀጠለ

በድንጋጌው ንኡስ አንቀፅ 1 መሰረት ለ3 ወራት ዘግይቶ ለቀረበ ታክስ ማስታወቂያ 20,000*3 ወር*5%= 3,000.00

- በድንጋጌው ንኡስ አንቀፅ 4 መሰረት የሚጣለው መቀጫ በማንኛውም ሁኔታ ቀጥሎ ከተመለከቱት ከዝቅተኛው ያነሰ አይሆንም በሚለው
- በንኡስ አንቀፅ “ሀ” መሰረት ብር 10,000.00
- በንኡስ አንቀፅ “ለ” መሰረት ብር 20,000*100% = 20,000
- በዚህ መሰረት የሚጣለው አስተዳደራዊ መቀጫ በንዑስ አንቀጽ 1 መሰረት የተሰላው መቀጫ ከንዑስ አንቀጽ 4 ሲነጻጸር ብር 3,000 ከብር 10,000 ወይም ከዝቅተኛው ያነሰ በመሆኑ በድንጋጌው መሰረት **ብር 10,000 ለታክስ ዘመኑ ቅጣት ይከፍላል ማለት ነው፡፡**

# ምሳሌ 3.

- አንድ ታክስ ከፋይ በታክስ ዘመኑ ያልከፈለው ወይም በቀሪነት የሚፈለግበት የታክስ መጠን ብር 4,000 ቢሆንና የታክስ ማስታወቂያዉን ለአራት ወራት አዘግይቶ ቢያቀርብ አስተዳደራዊ መቀጫው እንደሚከተለው ይሰላል።

የቀጠለ

**መልስ፡-** በድንጋጌ ተራ ቁጥር 12.1 መሠረት ለ4 ወራት ዘግይቶ ለቀረበ ታክስ ማስታወቂያ 4,000* 4ወር*5%= 800.00 (ዉሳኔ አማራጭ አንድ)

- በድንጋጌው ተራ ቁጥር 12.4 መሠረት የሚጣለው መቀጫ በማንኛውም ሁኔታ ቀጥሎ ከተመለከቱት **ከዝቅተኛው ያነሰ አይሆንም** በሚለው:-
- ብር 10,000፣
- በታክስ ማስታወቂያ ላይ መመልከት ከነበረበት የታክስ መጠን 100%፣
- **(ብር 4,000.00*100% = 4,000.00 (ዉሳኔ አማራጭ ሁለት)**
- በዚህ መሠረት የሚጣለው አስተዳደራዊ መቀጫ ተራ ቁጥር 12.1 መሰረት የተሰላው መቀጫ ከተራ ቁጥር 12.4 ጋር ሲነጻጸር ብር 800 ከብር 4,000 ያነሰ **በመሆኑ የሚከፍለዉ ቅጣት ብር 4,000 ይሆናል ማለት ነው።**

- **ምሳሌ 4፡-** የተጨማሪ እሴት ታክስ ተመዝጋቢ በሀምሌ 2015 ዓ.ም ብር 2,000,000 ሰብስቦ ገቢ ያላደረገውን ብር በመጋቢት 2016 ቢያመጣ የቅጣት ስሌቱ ስንት ይሆናል?

## የታክስ ማስታወቂያ ዘግይቶ ማቅረብ ስለሚያስከትለው ቅጣት (104)

**ምሳሌ 4፡-** የተጨማሪ እሴት ታክስ ተመዝጋቢ በሀምሌ 2015 ዓ.ም ብር 2,000,000 ሰብስቦ ገቢ ያላደረገውን ብር በጥር 2016 ቢያመጣ የቅጣት ስሌቱ እንደሚከተለው ይሆናል።

ስሌት፡-2,000,000 x 5%= 100,000 በድንጋጌው ንዑስ አንቀጽ 2 መሰረት ብር (50,000)

2,000,000 x 5%= 100,000

2,000,000 x 5%= 100,000

2,000,000 x 5%= 100,000

2,000,000 x 5%= 100,000

የቀጠለ

## የታክስ ማስታወቂያ ዘግይቶ ማቅረብ ስለሚያስከትለው ቅጣት

ጠቅላላ ቅጣት ብር 500,000 ሲሆን በተራ ቁጥር 2 ድንጋጌ መሰረት **ለመጀመሪያው የሂሳብ ጊዜ ወይም ከፊል ለሆነው ጊዜ የታክስ ማስታወቂያ ያላቀረበ ሰው** በተራ ቁጥር 1 ድንጋጌ መሰረት የሚከፍለው መቀጫ ከብር 50,000 አይበልጥም የሚል በመሆኑ በዚህ የሂሳብ ስሌት የመጀመሪያው የሂሳብ ጊዜ መስከረም በመሆኑ የመስከረም ወር ቅጣት ብር 50,000 ይሆናል ማለት ነው። በመሆኑም የታክስ ማስታወቂያ ዘግይቶ ለቀረበበት ጠቅላላ ወራት የሚቀጣው ቅጣት ብር **450,000 ይሆናል ማለት ነው።**

# <u>**ታክስን ዘግይቶ መክፈል**</u> የሚያስከትለው ቅጣት (105)

1. ማንኛውም ታክስ ከፋይ በታክስ መክፈያ ጊዜው ውስጥ ታክስ ሳይከፍል ከቀረ ለዘገየበት ጊዜ፡-

ሀ) የታክስ መክፍያ ጊዜው ከላፈ ከአንድ ወር በኋላ ባልተከፈለው ታክስ ላይ 5% (አምስት በመቶ) ፣እና

ለ) ከዚያ በኋላ ለዘገየበት ለእያንዳንዱ ሙሉ ወይም ከፊል ወር ባልተከፈለው ታክስ ላይ ተጨማሪ 2% (ሁለት በመቶ)፣ መቀጫ ይከፈላል።

# ታክስን ዘግይቶ መክፈል የሚያስከትለው ቅጣት (105)

2. በዚህ አንቀጽ መሠረት የሚጣለው የመቀጫ መጠን መቀጫው ከዋናው የታክስ ዕዳ መብለጥ የለበትም፡፡

3. መክፈል በማይገባው ታክስ ላይ ሳይከፈል በዘገየበት የተጣለ መቀጫ ታክስ ከፋዩ ቢቀጣ ባለሥልጣኑ ታክስ ከፋዩ በታክስ ሕግ መሠረት ሊከፍል ከሚገባው በላይ የከፈለ መሆኑን ሲያምንበት በብልጫ የተከፈለውን የገንዘብ መጠን ለታክስ ከፋዩ ይመለሳል፡፡

4. ይህ አንቀጽ ከተከፋይ ሂሣብ ላይ ተቀንሶ ከሚከፈል ታክስ ጋር በተገናኘ በሚጣል ቅጣት ላይ ተፈጻሚ አይሆንም፡፡

ጥያቄ ቁጥር 1. ABC plc የ2015 በጀት ዓመትን የንግድ ትርፍ ግብር በየካቲት 2016 ብር 35,000 የንግድ ትርፍ ግብር ለመክፈል ቢመጣ ታክስን ዘግይቶ መክፈል **የሚያስከትለው ቅጣት ስንት ብር ይቀጣል?**

# መልስ

- 35,000 x 5% = ብር 1,750 ህዳር
- 35,000 x 7 % = ብር 2,450 ታህሳስ
- 35,000 x 9 % = ብር 3,150 ጥር
- 35,000 x 11 % = ብር 3,850 የካቲት
- **ታክስን ዘግይቶ መክፈል የሚያስከትለው ቅጣት ብር 3,850 ይሆናል**

## ከተከፋይ ሂሣብ ላይ ተቀንሶ ከሚከፈል ታክስ ጋር በተገናኘ የሚጣል ቅጣት (የታክስ አስተዳደር አዋጅ አንቀፅ 106)

- በገቢ ግብር አዋጁ በተደነገገው መሠረት ከተከፋይ ሂሣብ ላይ ታክስ ቀንሶ ለባለሥልጣኑ ማስተላለፍ ያለበት ማንኛውም ሰው ሳይቀንስ የቀረው ወይም ቀንሶ ለባለሥልጣኑ **ያላስተላለፈውን ታክስ 10% (አሥር በመቶ) መቀጫ ይከፍላል።**
- ከላይ ለተመለከተው አፈጻጸም ለድርጅት ተፈጻሚ በሚሆንበት ጊዜ፣ በዚሁ ድንጋጌ መሠረት ከሚጣለው ቅጣት በተጨማሪ **የድርጅቱ ሥራ አስኪያጅ፣ ዋና የሂሳብ ሹም ወይም ታክስ ተቀንሶ መያዝ እንዳለበትና የተያዘውም ታክስ መከፈል እንዳለበት የማረጋገጥ ኃላፊነት** ያለበት ማንኛውም ሌላ የድርጅቱ ሠራተኛ **እያንዳንዳቸው ብር 2,000** (ሁለት ሺህ ብር) መቀጫ ይከፍላሉ።

## ❑መረጃ ያለመስጠት የሚያስከትለው ቅጣት፤

መረጃ የመስጠት ግዴታ ያለበት ባለሥልጣኑ በጽሑፍ ሲጠይቀው የተጠየቀውን መረጃ ያላቀረበ እንደሆነ መረጃውን ያልሰጠው ሰው ወይም መረጃ የተጠየቀው መ/ቤት የበላይ ኃላፊ 5ሺ ብር ይቀጣል።

# አስተዳደራዊ ቅጣቶች…

- ልዩ ልዩ ቅጣቶች

➢ ማንኛውንም ለውጥ ያላሳወቀ 20ሺ ሺ ብር ቅጣት ይከፍላል፡፡

➢ የመመስረቻ ጽሑፉን፣ መተዳደሪያ ደንቡን፣ የሽርክና ስምምነቱን፣ ወይም ሌላ የመመስረቻ ወይም የምዝገባ ሰነድ ወይም በእነዚህ ሰነዶች ላይ የተደረገውን ማንኛውም ማሻሻያ ሳያቀርብ የቀረ ድርጅት ሰነዱ ሳይቀርብ ለቀረበት ለእያንዳንዱ ወር ወይም የወሩ ከፊል ለሆነው ጊዜ 10ሺ ብር ቅጣት ይከፍላል፡፡

➢ የኦዲት ሪፖርቱን ለባለሥልጣኑ ያላቀረበ ማንኛውም ኦዲተር ሰነዱ ሳይቀርብ ለቀረበት ለእያንዳንዱ ወር ወይም የወሩ ከፊል ለሆነው ጊዜ ብር 10ሺ ብር ቅጣት ይከፍላል፡፡

## አስተዳደራዊ ቅጣቶች…

- በኢትዮጵያ ነዋሪ ካልሆነ ሰው ጋር የተደረገን ውል ያላሳወቀ፤ ሳያሳውቅ ለቀረበት ለእያንዳንዱ ቀን 1ሺ ብር ይቀጣል።
- ግንኙነት ካለው ሰዎች ጋር የሚያደርጋቸውን ግብይቶች ዝርዝር ጉዳይ ለባለሥልጣኑ ያልገለጸ ሰው ብር 100ሺ ብር ይቀጣል።

# 3.3. የታክስ ወንጀል ጉዳዮች የሚታዩበት ሥነ-ሥርዓት

- ❑ **ከታክስ ከፋይ መለያ ቁጥር ጋር የተገናኙ ወንጀሎች**

➢ ከ1 በላይ መለያ ቁጥር የወሰደ/ለመውሰድ የሞከረ፤ የመለያ ቁጥሩን ሌላ ሰው እንዲጠቀምበት የሰጠ፤ የሌላን ሰው መለያ ቁጥር የተጠቀመ፤ 20ሺ ብር እና ከ1-3 ዓመት ቀላል እሥራት ይቀጣል።

- ❑ **የሀሰት ወይም አሳሳች መግለጫዎች እና የተጭበረበሩ ሰነዶች**

ለባለሥልጣኑ፤ ሆነ ብሎ/በከባድ ቸልተኝነት፤ ሀሰተኛ/አሳሳች መግለጫ የሰጠ፤/ሊቀርብ የሚገባን መግለጫ መካተት የሚገባቸውን ነገሮች ያለበቂ ምክንያት ያስቀረ፤ የተጭበረበሩ ሰነዶችን ያቀረበ፤ ከ50ሺ-100ሺ ብር እና ከ3 ዓመት-15 ዓመት ጽኑ እሥራት ይቀጣል።

## ወንጀል...

- ➢ የታክስ ሕግ አስተዳደርን ያደናቀፈ/ለማደናቀፍ የሞከረ ከ10ሺ ብር በማያንስ ገንዘብ እና ከ3-5 ዓመት ጽኑ እሥራት ይቀጣል፡፡

❑ **ሥልጣን ሳይኖር ታክስ መሰብሰብ**

- ➢ ታክስ እንዲሰበስብ ሥልጣን ያልተሰጠው፤ ማንኛውንም ታክስ የሰበሰበ/ለመሰብሰብ ከሞከረ ከ50ሺ-75ሺ ብር እና ከ5-7 ዓመት ጽኑ እሥራት ይቀጣል፡፡

❑ **በታክስ ወንጀል መርዳት ወይም ማበረታታት**

በታክስ ሕግ "ዋና ወንጀል" አድራጊ ተብሎ የሚታወቅ ሌላ ሰው እንዲፈጽም የረዳ፣ ያበረታታ፣ ያገዘ፣ ያነሳሳ ወይም የተመሳጠረ እንደሆነ በዋናው ወንጀል አድራጊ ላይ የተጣለውን ቅጣት ይቀጣል፡፡

## ወንጀል…

- ከታክስ ይግባኝ ኮሚሽን ጋር የተያያዙ ወንጀሎች

➢ በታክስ ይግባኝ ኮሚሽን አባልነቱ ኃላፊነቱን በመፈጸም ላይ ያለን ሰው የሰደበ፤ ፈቃድ ሳይኖረው የኮሚሽኑን የሥራ ሂደት ያቋረጠ፤ የኮሚሽኑን የሥራ ሂደት ለማወክ በማሰብ በኮሚሽኑ ግቢ ውስጥ ወይም ኮሚሽኑ ባለበት አካባቢ ረብሻ የፈጠረ ወይም በረብሻው የተሳተፈ፤ ወይም በማናቸውም ሁኔታ የኮሚሽኑን ሥራ ያሰናከለ እንደሆነ፤ ከ500-3ሺ ብር ወይም ከ6 ወር-2 ዓመት ቀላል እሥራት ይቀጣል።

➢ ለኮሚሽኑ እያወቀ ሀሰተኛ/አሳሳች ማስረጃ የሰጠ ከ50ሺ ብር በማያንስ እና ከ3-5 ዓመት ጽኑ እሥራት ይቀጣል።

## ወንጀል…

- በኮሚሽኑ ፊት እንዲቀርብ/ለኮሚሽኑ ሰነድ እንዲያቀርብ/መረጃ እንዲሰጥ መጥሪያ ሲደርሰው ያለበቂ ምክንያት በመጥሪያው መሠረት ያልፈጸመ፤ በኮሚሽኑ ፊት ያለምንም በቂ ምክንያት ቃለ-መሃላ ለመፈጸም/እውነትን ለመመስከር ማረጋገጫ ለመስጠት ፈቃደኛ ያልሆነ፤ ኮሚሽኑ በሚያየው ጉዳይ ለቀረበለት ጥያቄ ያለ በቂ ምክንያት መልስ ለመስጠት ፈቃደኛ ያልሆነ፤ ከ300 ብር-3ሺ ብርና ከ6 ወር-2 ዓመት ቀላል እሥራት ይቀጣል።

### ❑ በታክስ ወኪሎች ስለሚፈፀም ወንጀል

- ያለፈቃድ የታክስ ወኪልነት አገልግሎት የሰጠ እንደሆነ ከአንድ ዓመት እስከ ሦስት ዓመት በሚደርስ ቀላል እሥራት ይቀጣል።

## 3.4. ሽልማቶች

ማንኛውም ሰው በመደበቅ፣ አሳንሶ በማሳወቅ፣ በማጭበርበር/በሌላ ተገቢ ባልሆነ መንገድ የሚፈፀምን የታክስ ስወራ አስመልክቶ ሊረጋገጥ የሚችል ተጨባጭና የማያሻማ መረጃ ለባለሥልጣኑ የሰጠ እንደሆነ፤ የተሰወረውን ታክስ መጠን እስከ 20% በሽልማት መልክ ታክሱ በሚሰበሰብበት ጊዜ ለዚህ ሰው ይሰጣል። ይህ በታክስ ስወራው ተግባር ላይ ለተሳተፈ፣ ወይም የታክስ ስወራውን ማሳወቅ የመደበኛ ሥራው አካል ለሆነ ሰው ተፈፃሚ አይሆንም።

### ሙከራ ሶስት

- በታክስ የሚፈጸሙ የአስተዳደራዊ እና የወንጀል ቅጣቶች እንዲሁም ሽልማቶች አብራሩ?

# ክፍል አራት

- የታክስ አስተዳደራዊ ቅጣት አነሳስ

  መመሪያ ቁጥር 189/2017

# ክፍል አራት፡- አስተዳደራዊ ቅጣት አነሳስ

## 4.1. ዝቅተኛ፣ መካከለኛ እና ከፍተኛ የቅጣት ደረጃ አነሳስ

- ከምዝገባ እና ስረዛ ጋር የተያያዙ ቅጣቶች (የታክስ አስተዳደር አዋጅ አንቀፅ **101)**
- ከታክስ ከፋይ መለያ ቁጥር ጋር የተገናኘ ቅጣት (የታክስ አስተዳደር አዋጅ አንቀፅ **103)**
- ታክስን አሳንሶ ማሳወቅ የሚያስከትለው ቅጣት (የታክስ አስተዳደር አዋጅ አንቀፅ **109)**
- በታክስ ወኪል ላይ ስለሚጣል ቅጣት(የታክስ አስተዳደር አዋጅ አንቀፅ **112)**

| ተ.ቁ | ፍሬ፣ወለድና መቀጮ የተከፈለበት ግዜ | የቅጣት አነሳስ ምጣኔ በደረጃ መሰረት | | |
|---|---|---|---|---|
| | | ዝቅተኛ | መካከለኛ | ከፍተኛ |
| 1 | **ታክስ ከፋዩ፤- ማስታወቅያ፣የቅሬ፣የፍ/ቤት ውሳኔ ደርሶት** | | | |
| | በ30 ቀናት ውስጥ ቀርቦ ከከፈለ | 90 | 80 | 70 |
| | ውል ገብቶ በ6 ወራት ውስጥ ከፍሎ ካጠናቀቀ | 80 | 70 | 60 |
| | ውል ገብቶ ከ6 ወራት በላይ ከፈጀበት | 70 | 60 | 50 |
| 2 | **ባለመክፈሉ ማስጠንቀቂያ ሳይደርሰው ንብረቱ ከተያዘ በኋላ** | | | |
| | በ1 ግዜ አጠቃሎ ከከፋለ | 80 | 70 | 60 |
| | ውል ገብቶ በ6 ወራት **ውስጥ** ከከፈለ | 70 | 60 | 50 |
| | ውል ገብቶ ከ6 ወራት **በላይ** ከፈጀበት | 60 | 50 | 40 |
| 3 | **ባለመክፈሉ** ሃብቱ ተይዞ የመዮዣ ማስጠንቀቅያ ከተሰጠ በኋላ | | | |
| | በ1 ወር ውስጥ አጠቃሎመቶ ከከፈለ | 70 | 60 | 50 |
| | ውል ገብቶ በ6 ወራት **ውስጥ** ከከፈለ | 60 | 50 | 40 |
| | ውል ገብቶ ከ6 ወራት **በላይ** ከፈጀበት | 50 | 40 | 30 |

| ተ.ቁ | ፍሬ፣ወለድና መቀጮ የተከፈለበት ግዜ | የቅጣት አነሳስ ምጣኔ በደረጃ መሰረት | | |
|---|---|---|---|---|
| | | ዝቅተኛ | መካከለኛ | ከፍተኛ |
| 4 | **ባለ መክፈሉ ሃብቱ ከተያዘ በኋላ ጫረታ ሳይወጣበት** | | | |
| | በ 1 ግዜ ቀርቦ ከከፈለ | 60 | 50 | 40 |
| | ውል ገብቶ በ6 ወራት ውስጥ ከፍሎ ካጠናቀቀ | 50 | 40 | 30 |
| | ውል ገብቶ ከ6 ወራት በላይ ከፈጀበት | 40 | 30 | 20 |
| 5 | **ታከስ ከፋዩ የሚፈለግበትን ታከስ ጫረታ ከወጣበት** በኋላ | | | |
| | በ10 ቀናት ውስጥ አጠናቆ ከከፋለ | 50 | 40 | 30 |
| | ውል ገብቶ በ6 ወራት **ውስጥ** ከከፈለ | 40 | 30 | 20 |
| | ውል ገብቶ ከ6 ወራት **በላይ** ከፈጀበት | 30 | 20 | 10 |

## 4.1. ዝቅተኛ፣ መካከለኛ እና ከፍተኛ የቅጣት ደረጃ አነሳስ

- **ዝቅተኛ የቅጣት ደረጃ (ከ30-90%) ይነሳል**

- ከምዝገባ እና ስረዛ ጋር የተያያዙ ቅጣቶች (የታክስ አስተዳ

  አዋጅ አንቀፅ 101)

- ከታክስ ከፋይ መለያ ቁጥር ጋር የተገናኝ ቅጣት (የታ

  አስተዳደር አዋጅ አንቀፅ 103)

- ታክስን አሳንሶ ማሳወቅ የሚያስከትለው ቅጣት (የታክስ አስተዳ

  አዋጅ አንቀፅ 109)

- በታክስ ወኪል ላይ ስለሚጣል ቅጣት(የታክስ አስተዳደር አ

  አንቀፅ 112)



# ክፍል አራት:- አስተዳደራዊ ቅጣት አነሳስ

## 4.1. ዝቅተኛ፣ መካከለኛ እና ከፍተኛ የቅጣት ደረጃ አነሳስ

- **መካከለኛ የቅጣት ደረጃ (ከ20-80%) ይነሳል**

- ታክስን ዘግይቶ መክፈል የሚያስከትለው ቅጣት (ታ.አ.አንቀ.105)

- ከተከፋይ ሂሣብ ላይ ተቀንሶ ከሚከፈል ታክስ ጋር በተገናኘ የሚጣል ቅጣት (ታ.አስ.አ.አንቀ 106)

- ልዩ ልዩ ቅጣቶች ታ.አ.አንቀ.114(ከንዑአንቀ 1እስከ 6) የአድራሻ ለውጥ ያላሳወቀ ታክስ ከፋይ ብር 20ሺ እና ግንኙነት ካለው ሰዎች ጋር የሚያደርጋቸውን ግብይቶች ዝርዝር ጉዳይ ለባለሥልጣኑ ያልገለጸ ሰው ብር 10ሺ ሲቀጣ።

| ተ.ቁ | ፍሬ፣ወለድና መቀጮ የተከፈለበት ግዜ | የቅጣት አነሳስ ምጣኔ በደረጃ መሰረት | | |
|---|---|---|---|---|
| | | ዝቅተኛ | መካከለኛ | ከፍተኛ |
| 1 | **ታክስ ከፋዩ፤- ማስታወቅያ፣የቅሬ፣የፍ/ቤት ውሳኔ ደርሶት** | | | |
| | በ30 ቀናት ውስጥ ቀርቦ ከከፈለ | 90 | 80 | 70 |
| | ውል ገብቶ በ6 ወራት ውስጥ ክፍሎ ካጠናቀቀ | 80 | 70 | 60 |
| | ውል ገብቶ ከ6 ወራት በላይ ከፈጀበት | 70 | 60 | 50 |
| 2 | **ባለመክፈሉ ማስጠንቀቂያ ሳይደርሰው ንብረቱ ከተያዘ በኋላ** | | | |
| | በ1 ግዜ አጠቃሎ ከከፋለ | 80 | 70 | 60 |
| | ውል ገብቶ በ6 ወራት **ውስጥ** ከከፈለ | 70 | 60 | 50 |
| | ውል ገብቶ ከ6 ወራት **በላይ** ከፈጀበት | 60 | 50 | 40 |
| 3 | **ባለመክፈሉ** ሃብቱ ተይዞ የመየዣ ማስጠንቀቅያ ከተሰጠ በኋላ | | | |
| | በ1 ወር ውስጥ አጠቃሎመቶ ከከፈለ | 70 | 60 | 50 |
| | ውል ገብቶ በ6 ወራት **ውስጥ** ከከፈለ | 60 | 50 | 40 |
| | ውል ገብቶ ከ6 ወራት **በላይ** ከፈጀበት | 50 | 40 | 30 |
| 4 | **ባለ መክፈሉ ሃብቱ ከተያዘ በኋላ ጨረታ ሳይወጣበት** | | | |
| | በ 1 ግዜ ቀርቦ ከከፈለ | 60 | 50 | 40 |
| | ውል ገብቶ በ6 ወራት ውስጥ ክፍሎ ካጠናቀቀ | 50 | 40 | 30 |
| | ውል ገብቶ ከ6 ወራት በላይ ከፈጀበት | 40 | 30 | 20 |
| 5 | **ታክስ ከፋዩ የሚፈለግበትን ታክስ ጫረታ ከወጣበት** በኋላ | | | |
| | በ10 **ቀናት ውስጥ** አጠናቆ ከከፋለ | 50 | 40 | 30 |
| | ውል ገብቶ በ6 ወራት **ውስጥ** ከከፈለ | 40 | 30 | 20 |
| | ውል ገብቶ ከ6 ወራት **በላይ** ከፈጀበት | 30 | 20 | 10 |

- **መካከለኛ የቅጣት ደረጃ (ከ20-80%) ይነሳል**
- ታክስን ዘግይቶ መክፈል የሚያስከትለው ቅጣት (የታክስ አስተዳደር አዋጅ አንቀፅ 105)
- ከተከፋይ ሂሣብ ላይ ተቀንሶ ከሚከፈል ታክስ ጋር በተገናኘ የሚጣል ቅጣት (የታክስ አስተዳደር አዋጅ አንቀፅ 106)
- ማንኛውንም ለውጥ ያላሳወቀ 20ሺ ብር ቅጣት የሚከፍለው ቅጣት(የታክስ አስተዳደር አዋጅ አንቀፅ 114)
- የመመስረቻ ጽሑፉን፣ መተዳደሪያ ደንቡን፣ የሽርክና ስምምነቱን፣ ወይም ሌላ የመመስረቻ ወይም የምዝገባ ሰነድ ወይም በእነዚህ ሰነዶች ላይ የተደረገውን ማንኛውም ማሻሻያ ሳያቀርብ የቀረ ድርጅት ሰነዱ ሳይቀርብ ለቀረበት ለእያንዳንዱ ወር ወይም የወሩ ከፊል ለሆነው ጊዜ 10ሺ ብር ቅጣት ቅጣት የሚከፍለው ቅጣት(የታክስ አስተዳደር አዋጅ አንቀፅ 114)



- የኦዲት ሪፖርቱን ለባለሥልጣኑ ያላቀረበ ማንኛውም ኦዲተር ሰነዱ ሳይቀርብ ለቀረበት ለእያንዳንዱ ወር ወይም የወሩ ክፊል ለሆነው ጊዜ ብር 10ሺ ብር ቅጣት የሚከፍለው ቅጣት(የታክስ አስተዳደር አዋጅ አንቀፅ 114)
- በኢትዮጵያ ነዋሪ ካልሆነ ሰው ጋር የተደረገን ውል ያላሳወቀ፣ ሳያሳውቅ ለቀረበት ለእያንዳንዱ ቀን 1ሺ ብር ቅጣት የሚከፍለው ቅጣት (የታክስ አስተዳደር አዋጅ አንቀፅ 114)
- ግንኙነት ካለው ሰዎች ጋር የሚያደርጋቸውን ግብይቶች ዝርዝር ጉዳይ ለባለሥልጣኑ ያልገለጸ ሰው ብር 100ሺ ብር ቅጣትየሚከፍለው ቅጣት (የታክስ አስተዳደር አዋጅ አንቀፅ 114)
- ፈቃድ ሳይኖረው የኤክሣይዝ ታክስ የሚከፈልባቸውን ዕቃዎች የሚያመርት ሊከፍል የሚገባውን የኤክሣይዝ ታክስ እጥፍ ቅጣት (በኤክሳይዝ ታክስ አዋጅ ቁጥር 1186/2012 አንቀጽ 38)



# ዝቅተኛ፣ መካከለኛ እና ከፍተኛ የቅጣት ደረጃ አነሳስ...

- **ከፍተኛ የቅጣት ደረጃ** (ከ10-70%) ይነሳል

- ሰነዶችን ባለመያዝ የሚጣል ቅጣት፣ (ታ.አ.አንቀ.102)
- ታክስን ማስታወቂያ ዘግይቶ ማሳወቅ (ታ.አ.አንቀ.104/
- ከተጨማሪ እሴት ታክስ ጋር የተያያዙ ቅጣቶች(ታ.አ.አንቀ.107) ሆን ብሎ በግብይቱ ላይ መከፈል የሚገባውን VAT ለማሳነስ/ በግብይቱ ላይ ተመላሽ የሚደረገውን የታክስ መጠን ለመጨመር በማሰብ ትክክለኛ ያልሆነ የታክስ ደረሰኝ የሰጠ ብር 50ሺ ሲቀጣ፤
- ታክስ ደረሰኝ ባለመስጠት ብር 50ሺ ሲቀጣ እና ታክስን በመሸሸ ሲቀጣ፤ (ታ.አ.አንቀ.108)
- ታክስን በመሸሸ የሚጣለው ቅጣት(ታ.አ.አንቀ.110)
- የኤሌክትሮኒክስ የታክስ ሥርዓትን ባለመከተል የሚጣል ቅጣት(ታ.አ.አንቀ.111)
- ለታክስ ሰብሳቢው የተጠየቀ መረጃ ባለመስጠት 5ሺ ሲቀጣ። (ታ.አ.አንቀ.114/7)

| ተ.ቁ | ፍሬ፣ወለድና መቀጮ የተከፈለበት ግዜ | የቅጣት አነሳስ ምጣኔ በደረጃ መሰረት | | |
|---|---|---|---|---|
| | | ዝቅተኛ | መካከለኛ | ከፍተኛ |
| 1 | **ታክስ ከፋዩ፤- ማስታወቅያ፣የቅሬ፣የፍ/ቤት ውሳኔ ደርሶት** | | | |
| | በ30 ቀናት ውስጥ ቀርቦ ከከፈለ | 90 | 80 | 70 |
| | ውል ገብቶ በ6 ወራት ውስጥ ከፍሎ ካጠናቀቀ | 80 | 70 | 60 |
| | ውል ገብቶ ከ6 ወራት በላይ ከፈጀበት | 70 | 60 | 50 |
| 2 | **ባለመክፈሉ ማስጠንቀቂያ ሳይደርሰው ንብረቱ ከተያዘ በኋላ** | | | |
| | በ1 ግዜ አጠቃሎ ከከፋለ | 80 | 70 | 60 |
| | ውል ገብቶ በ6 ወራት **ውስጥ** ከከፈለ | 70 | 60 | 50 |
| | ውል ገብቶ ከ6 ወራት **በላይ** ከፈጀበት | 60 | 50 | 40 |
| 3 | **ባለመክፈሉ** ሃብቱ ተይዞ የመየዣ ማስጠንቀቅያ ከተሰጠ በኋላ | | | |
| | በ1 ወር ውስጥ አጠቃሎመቶ ከከፈለ | 70 | 60 | 50 |
| | ውል ገብቶ በ6 ወራት **ውስጥ** ከከፈለ | 60 | 50 | 40 |
| | ውል ገብቶ ከ6 ወራት **በላይ** ከፈጀበት | 50 | 40 | 30 |
| | | | | |

| ተ.ቁ | ፍሬ፣ወለድና መቀጮ የተከፈለበት ግዜ | የቅጣት አነሳስ ምጣኔ በደረጃ መሰረት | | |
|---|---|---|---|---|
| | | ዝቅተኛ | መካከለኛ | ከፍተኛ |
| 4 | **ባለ መክፈሉ ሃብቱ ከተያዘ በኋላ ጫረታ ሳይወጣበት** | | | |
| | በ 1 ግዜ ቀርቦ ከከፈለ | 60 | 50 | 40 |
| | ውል ገብቶ በ6 ወራት ውስጥ ከፍሎ ካጠናቀቀ | 50 | 40 | 30 |
| | ውል ገብቶ ከ6 ወራት በላይ ከፈጀበት | 40 | 30 | 20 |
| 5 | **ታክስ ከፋዩ የሚፈለግበትን ታክስ ጫረታ ከወጣበት** በኋላ | | | |
| | በ10 **ቀናት ውስጥ** አጠናቆ ከከፋለ | 50 | 40 | 30 |
| | ውል ገብቶ በ6 ወራት **ውስጥ** ከከፈለ | 40 | 30 | 20 |
| | ውል ገብቶ ከ6 ወራት **በላይ** ከፈጀበት | 30 | 20 | 10 |

## ❑ ከፍተኛ የቅጣት ደረጃ (ከ10-70%) ይነሳል



- ሰነዶችን ባለመያዝ የሚጣል ቅጣት (የታክስ አስተዳደር አዋጅ አንቀፅ 102)
- የታክስ ማስታወቂያ ዘግይቶ ማቅረብ ስለሚያስከትለው ቅጣት (የታክስ አስተዳደር አዋጅ አንቀፅ 104)
- ከተጨማሪ እሴት ታክስ ጋር የተያያዙ ቅጣቶች (የታክስ አስተዳደር አዋጅ አንቀፅ 107)
- ታክስን በመሸሸ የሚጣለው ቅጣት (የታክስ አስተዳደር አዋጅ አንቀፅ 110)
- የኤሌክትሮኒክስ የታክስ ሥርዓትን ባለመከተል የሚጣል ቅጣት(የታክስ አስተዳደር አዋጅ አንቀፅ 111)
- መረጃ ያለመስጠት የሚያስከትለው ቅጣት(የታክስ አስተዳደር አዋጅ አንቀፅ 114(7))
- የተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ ቁጥር 1341/2016 አንቀጽ 66 መሰረት የሚጣለው ቅጣት

## 4.2. የአስተዳደራዊ ቅጣት በከፊል የሚነሳበት መስፈርት እና መጣኔ

| ተ.ቁ | ፍሬ፣ወለድና መቀጮ የተከፈለበት ግዜ | የቅጣት አነሳስ ምጣኔ በደረጃ መሰረት | | |
|---|---|---|---|---|
| | | ዝቅተኛ | መካከለኛ | ከፍተኛ |
| 1 | **ታክስ ከፋዩ፤- ማስታወቅያ፣የቅሬ፣የፍ/ቤት ውሳኔ ደርሶት** | | | |
| | በ30 ቀናት ውስጥ ቀርቦ ከከፈለ | 90 | 80 | 70 |
| | ውል ገብቶ በ6 ወራት ውስጥ ከፍሎ ካጠናቀቀ | 80 | 70 | 60 |
| | ውል ገብቶ ከ6 ወራት በላይ ከፈጀበት | 70 | 60 | 50 |
| 2 | **ባለመክፈሉ ማስጠንቀቂያ ሳይደርሰው ንብረቱ ከተያዘ በኋላ** | | | |
| | በ1 ግዜ አጠቃሎ ከከፋለ | 80 | 70 | 60 |
| | ውል ገብቶ በ6 ወራት **ውስጥ** ከከፈለ | 70 | 60 | 50 |
| | ውል ገብቶ ከ6 ወራት **በላይ** ከፈጀበት | 60 | 50 | 40 |
| 3 | **ባለመክፈሉ** ሃብቱ ተይዞ የመየዣ ማስጠንቀቅያ ከተሰጠ በኋላ | | | |
| | በ1 ወር ውስጥ አጠቃሎመቶ ከከፈለ | 70 | 60 | 50 |
| | ውል ገብቶ በ6 ወራት **ውስጥ** ከከፈለ | 60 | 50 | 40 |
| | ውል ገብቶ ከ6 ወራት **በላይ** ከፈጀበት | 50 | 40 | 30 |

# በከፊል የሚነሳበት መስፈርት እና መጣኔ...

| ተ.ቁ | ፍሬ፣ወለድና መቀጮ የተከፈለበት ግዜ | የቅጣት አነሳስ ምጣኔ በደረጃ መሰረት | | |
|---|---|---|---|---|
| | | ዝቅተኛ | መካከለኛ | ከፍተኛ |
| 4 | ባለ መክፈሉ ሃብቱ ከተያዘ በኋላ ጨረታ ሳይወጣበት | | | |
| | በ 1 ግዜ ቀርቦ ከከፈለ | 60 | 50 | 40 |
| | ውል ገብቶ በ6 ወራት ውስጥ ከፍሎ ካጠናቀቀ | 50 | 40 | 30 |
| | ውል ገብቶ ከ6 ወራት በላይ ከፈጀበት | 40 | 30 | 20 |
| 5 | ታክስ ከፋዩ የሚፈለግበትን ታክስ ጨረታ ከወጣበት በኋላ | | | |
| | በ10 ቀናት ውስጥ አጠናቆ ከከፋለ | 50 | 40 | 30 |
| | ውል ገብቶ በ6 ወራት **ውስጥ** ከከፈለ | 40 | 30 | 20 |
| | ውል ገብቶ ከ6 ወራት **በላይ** ከፈጀበት | 30 | 20 | 10 |

## 4.3. አስተዳደራዊ ቅጣት ሙሉ በሙሉ የሚነሳበት አግባብ

- ታክስ ከፋዩ የታክስ ግዴታውን በመክፍያ ጊዜው እንዳይከፍል የሚያደርግ ከአቅም በላይ የሆነ ምክንያት ያጋጠመው ከሆነ፤(ሰው ሰራሽ ወይም የተፈጥሮ አደጋ ጽኑ ህመም)
- የድርጅቱ የንግድ ሥራ ሊቀጥል የማይችል እና የከሠረ (bankrupt) መሆኑ በፍ/ቤት ሲረጋገጥ፤
- ባለሥልጣኑ የታክስ ከፋዩን ሒሳብ ከመመርመሩ በፊት ታክስ ከፋዩ ስህተቱን በራሱ ተነሳሽነት ያረመ እንደሆነና በተሻሻላው የታክስ ስሌት መሠረት ፍሬ ታክስና ወለድ ከከፈለ፤
- ከንብረቱ 20 በመቶ እና ከዚያ በላይ በተፈጥሮ ወይም በሰው በአደጋ ሰራሽ ምክንያት የወደመበት መሆኑን የሚገልጽ ማስረጃ ከሚመለከተው የመንግሥት ተቋም ያቀረበ ከሆነ፤



አስተዳደራዊ ቅጣት ሙሉ በሙሉ የሚነሳበት አግባብ ----------

- ለቅጣቱ ምክንያት የሆነው ታክስ ባለስልጣኑ መስሪያ ቤቱ በፈጠረው የአሰራር ስህተት መሆኑ ከተረጋገጠ፤
- ከወርሃዊ ማሳወቂያ ጋር በተያያዘ በመክፊያ ጊዜው ግብር ከፋዩ ባንክ ገቢ በሚያደርግበት ጊዜ በወቅቱ ቀርቦ ደረሰኝ ባለማስቆረጥ ምክንያት በሲስተም የሚሰላው ቅጣት፤
- ታክስ ከፋዩ የታክስ ውሳኔ ማስታወቂያ ወይም የግብር ይግባኝ ወይም የፍርድ ቤት ውሳኔ በደረሰው 30 ቀናት ውስጥ ታክሱን ወለድ እንዲሁም በመካከለኛ ወይም በከፍተኛ ደረጃ የማይነሳውን ቅጣት ሙሉ በሙሉ ከከፈሉ በታክስ ውሳኔ ውስጥ የሚገኝና በዝቅተኛ ደረጃ የተመደበ አስተዳራዊ ቅጣት ካለ ሙሉ በሙሉ ይነሳል፤



- በከፍተኛ እና በመካከለኛ ደረጃ የተመደበ መቀጫ ባይኖርም ከታክስና ወለድ ጋር በዝቅተኛ ደረጃ የተመደበ መቀጫ የተወሰነ ከሆነ ታክስ

## 4.4. አስተዳደራዊ ቅጣትን በልዩ ሁኔታ ስለማንሳት

- በኢኮኖሚያዊ፣ አስተዳደራዊ ወይም ማህበራዊ ምክንያቶች የታክስ ባለሥልጣኑ ወይም በሚወክለው የበላይ ኃላፊ በልዩ ሁኔታ በታክስ ከፋዩ ጥያቄ ወይም ባለሥልጣኑ የራስ ተነሳሽነት መሠረት የተጣለን አስተዳደራዊ ቅጣት በልዩ ሁኔታ ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል ሊያነሳ ይችላል።



## 4.5. በክፍያ ስምምነት ጊዜ ቅጣት አነሳስ

በስምምነቱ መሠረት ፍሬ ታክሱንና ወለዱን ከፍሎ ማጠናቀቁ ሲረጋገጥ መቀጫው እንዲነሳ ይደረጋል።

## 4.6. አስተዳደራዊ ቅጣትን ይነሳልኝ ጥያቄ አቀራረብ

- አስተዳደራዊ ቅጣት የተወሰነበት ሰው/ድርጅት ቅጣቱ እንዲነሳለት ምክንያቱን በመግለጽ ለባለስልጣኑ ቅ/ጽ/ቤት የታክስ ዕዳ አስተዳደር የሥራ ሂደት አሰተባባሪ ወይም የታክስ ኦፕሬሽን የሥራ ሂደት መሪ ወይም የታክስ ማዕከል አሰተባባሪ በጽሑፍ ማመልከት አለበት፡፡
- የክፍያ ጊዜ ማራዘሚያ ስምምነት የገቡ ፍሬ ታክሱን፣ ወለዱንና የማይነሳውን ቅጣት ከፍለው ከጨረሱ ማመልከቻ ማቅረብ ሳያስፈልግ ቅጣቱ ይነሳል፡፡

## 4.7.አስተዳደራዊ ቅጣትን የማንሳት ሥልጣን

- የታክስ ዕዳ አስተዳደር የሥራ ሂደት አስተባባሪ
- የታክስ ኦፕሬሽን የሥራ ሂደት መሪ
- የታክስ ማዕከል አስተባባሪ

# 4.7. የማይነሳ አስተዳደራዊ ቅጣት

- የጡረታ መዋጮ እና የከፍተኛ ትምህርት ወጪ መጋራት በወቅቱ ባለመከፈል የተጣለ ቅጣት አይነሳም።
- በዘገየ የታክስ ክፍያ ላይ የሚታሰብ ወለድ የሚነሳ ወይም ቀሪ የሚደረግ አይሆንም።



**ሙከራ አራት**

- አስተዳደራዊ ቅጣት በከፊል ወይም ሙሉ በሙሉ የሚነሳባቸውን እና የማይነሳባቸውን ምክንያቶች ዘርዝሩ?

ማጠቃለያ

ከታክስ ጋር በተገናኘ የሚፈጠር አለመግባባት፣ የታክስ አስተዳደር እና የወንጀል ቅጣቶች እንዲሁም አስተዳደራዊ ቅጣት አነሳስ በዚህ ሥልጠና የተዳሰሱት ዋና ዋና ርዕሰ ጉዳዮች ናቸው። እነዚህን ርዕሰ ጉዳዮች ወደ ተግባር መቀየር የገቢዎች ሚኒስቴርን እና የግብር ከፋዩን ግንኙነት ሰላማዊ ያደርገዋል።



## ማጣቀሻ

- በፌደራል የታክስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 983/2008
- አስተዳደራዊ ቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 9/2011
- የታክስ ውሳኔ ቅሬታ አጣሪ ጽ/ቤት አሠራርን መ.ቁ. 171/2013
- የታክስ አስተዳደራዊ ቅጣት አነሳስ መመሪያ ቁጥር 189/2017
- Federal Democratic Republic of Ethiopia

  Federal Tax Administration Proclamation

  No. 983/2016 Technical Notes


CanStock
© Can Stock Photo - csp15962721


THANK
YOU
alamy stock photo